# የኢሚግሬሽን ማጭበርበሮችን እንዴት ማስወገድ እና እርዳታ ማግኘት እንደሚቻል

አጭበርባሪዎች የኢሚግሬሽን ሂደት ውስብስብ እንደሆነ ያውቃሉ። እገዛ የሚፈልጉ ሰዎችን ለመበዝበዝ የሚያስከትለውን ግራ መጋባት ይጠቀማሉ። አንዳንድ የተለመዱ የኢሚግሬሽን ማጭበርበሮች ምን እንደሆኑ፣ እነሱን እንዴት መለየት እና ማስወገድ እንደሚቻል እና እውነተኛ እርዳታ ከየት ማግኘት እንደሚችሉ አንዳንድ ምሳሌዎች እነሆ።

## የኢሚግሬሽን ማጭበርበሮች ምሳሌዎች

### ኖታሪዮ ወይም የኢሚግሬሽን አማካሪ ማጭበርበሮች

በዩናይትድ ስቴትስ የኢሚግሬሽን ምክር ሊሰጥዎ የሚችለው የኢሚግሬሽን ጠበቃ አሊያም በዩኤስ የፍትህ መምሪያ (U.S. Department of Justice, DOJ) ስልጣን ያለው ግለሰብ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ አጭበርባሪዎች እራሳቸውን ኖታሪዮ፣ ኖታሪይ ፐብሊክ፣ አካውንታንት ወይም አማካሪ ብለው በመጥራት ስደተኞችን ግራ ለማጋባት ይጥራሉ። በላቲን አሜሪካ ሀገራት ኖታሪዮ ወይም ኖታሪይ ፐብሊክ የሚለው ቃል ግለሰቡ ጠበቃ ነው ወይም የሕግ ስልጣና አለው ማለት ነው፣ ይሁን እንጂ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ይህ እውነት አይደለም።

**እውቅና ላለው ድርጅት የሚሰሩ በዩኤስ የፍትህ ዲፓርትመንት እውቅና የተሰጣቸው ጠበቆች እና ሰዎች ብቻ የህግ ምክር ሊሰጡዎት ይችላሉ።**

ሌላ ማንኛውም ሰው ገንዘብዎን ብቻ እየወሰደ ነው። አንዳንድ ጊዜ፣ የእነሱ መጥፎ ምክር በህጋዊ መንገድ የመሰደድ ወይም ህጋዊ ሁኔታዎን የማስተካከል እድልዎ ላይ ተጽዕኖ ያደርሳል። DOJ ሙሉ እውቅና ያላቸው ግለሰቦች እና እውቅና ያላቸው ድርጅቶች ዝርዝር አለው።

የnotario ማጭበርበሮችን እንዴት መለየት እና ማስወገድ እንደሚችሉ የበለጠ ለማወቅ፣ ይህንን ግራፊክ ኖቭል በእንግሊዝኛ ቋንቋ ያንብቡ፣ በስፓኒሽም ይገኛል። በማህበረሰብዎ ውስጥ ለማሰራጨት ነፃ ቅጂዎችን ይዘዙ።

### ማወቅ ያለብዎት፡-

- ለኢሚግሬሽን ወይም ለህጋዊ እርዳታ ወደ notario፣ አካውንታንት ወይም አማካሪ አይሂዱ። እውነተኛ እገዛን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ከታች ያለውን ምክር ይመልከቱ።
- ባዶ የኢሚግሬሽን ቅጾችን፣ ወይም ስለእርስዎ ወይም ስለሁኔታዎ የተሳሳተ መረጃ ያላቸውን ቅጾች አይፈርሙ። ሐቀኛ ያልሆነ ኖታሪዮ፣ አካውንታንት ወይም አማካሪ ይህን እንዲያደርጉ ሊጠይቅዎት ይችላል።
- ለኢሚግሬሽን ቅጾች አይክፈሉ። ከዩኤስ ዜግነትና ኢሚግሬሽን አገልግሎት (U.S. Citizenship and Immigration Services, USCIS) የሚመጡ ኦፊሴላዊ ቅጾች ነጻ ናቸው።
- አንድ ኖታሪዮ ወይም ሌላ ሰው ኦርጅናል ሰነዶችዎን እንዲይዙ አይፍቀዱ።

# የውሸት የኢሚግሬሽን ድረ ገጾች

የኢሚግሬሽን እገዛን በሚፈልጉበት ጊዜ ከ USCIS ጋር የተገናኙ የሚመስሉ ድረ-ገጾችን ሊያገኙ ይችላሉ — ግን እነሱ አይደሉም። እንደ “ዩኤስ ኢሚግሬሽን” ያሉ ስሞችን ሊጠቀሙ እና የአሜሪካን ባንዲራዎች ወይም የነጻነት ሃውልት ምስሎችን ሊያሳዩ ይችላሉ። ነገር ግን የድረ-ገጹ አድራሻ በ .gov ካላለቀ፣ የፌዴራል መንግስት ድረ-ገጽ **አይደለም** እና ከUSCIS ጋር አልተገናኘም ማለት ነው። ድረገጹ መንግስት በነፃ ለሚሰጣቸው ቅጾች ሊያስከፍልዎት ይችላል፣ እና የግል መረጃዎንም ሊሰርቅ ይችላል።

## ማወቅ ያለብዎት፡-

- እውነተኛ የአሜሪካ መንግስት ድረ-ገጽ አድራሻዎች በ .gov ያበቃሉ።
- የ USCIS ቅጾች ነፃ ናቸው። የመንግስት የኢሚግሬሽን ቅጾችን ለማውረድ መክፈል ካለብዎት፣ በህጋዊ ድህረ ገጽ ላይ አይደሉም።
- እውነተኛ የኢሚግሬሽን መረጃ በ USCIS ድረገጽ ላይ ያገኛሉ።

# የብዝሃነት ሎተሪ (Diversity Lottery) ማጭበርበሮች

የዩኤስ ስቴት ዲፓርትመንት (U.S. Department of State) የብዝሃነት ቪዛ ፕሮግራምን (Diversity Visa Program) ያስተዳድራል። አንዳንድ ሰዎች ይህንን ፕሮግራም “የቪዛ ሎተሪ” ብለው ይጠሩታል። ለመግባት ነፃ ነው። በዘፈቀደ የተመረጡ አሸናፊዎች፣ ህጋዊ ቋሚ ነዋሪ ለመሆን ለማመልከት እድሉን ያሸንፋሉ። ነገር ግን አጭበርባሪዎች ለፕሮግራሙ ለማመልከት ገንዘብ በማስከፈል፣ ልዩ መዳረሻ እንደሚያገኙ ቃል በመግባት ወይም ሎተሪ የማሸነፍ እድላቸውን ለመጨመር ቃል በመግባት ሰዎችን ለማታለል ይሞክራሉ። ይሁንና ምንም ልዩ መዳረሻ የለም፤ እናም ማንም የማሸነፍ እድልዎን ሊጨምር አይችልም።

## ማወቅ ያለብዎት፡-

- ቪዛ ሎተሪ መገባት መግባት የሚችሉ ይሆናል
  - በዓመት አንድ ጊዜ **ብቻ**
  - **በ** dvprogram.state.gov**ብቻ**
  - **ብቁ** ከሆኑ አገር የመጡ እና የትምህርት ወይም የሥራ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ከሆነ ብቻ

- ለቪዛ ሎተሪ ለማመልከት መክፈል አያስፈልግም።
- አሸናፊዎቹ በዘፈቀደ የሚመረጡ ሲሆን ማንም በውጤቱ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳርፍ አይችልም።
- የምዝገባዎን ሁኔታ በ dvprogram.state.gov ላይ **ብቻ** ማግኘት የሚችሉ ይሆናል።

## በስደተኞች ላይ የሚደረጉ ማጭበርበሮች

ስደተኞች — ከጦርነት፣ ከጭቆና ወይም ከተፈጥሮ አደጋ ለማምለጥ አገራቸውን ለቀው ለመውጣት የሚገደዱ ሰዎች ናቸው — እንዲሁም የማጭበርበሪያ ኢላማዎች ናቸው። ስደተኞች ከሌሎች ስደተኞች የተለየ ህጋዊ ሁኔታ አላቸው፣ ነገር ግን አጭበርባሪዎች ግድ የላቸውም። አጭበርባሪዎች ለስደተኞች፣ ለምሳሌ፣ ለልዩ የመንግስት የገንዘብ እርዳታ ብቁ እንደሆኑ ነገር ግን መጀመሪያ መክፈል እንዳለባቸው ይነግሩዋቸዋል። ወይም አጭበርባሪዎች ከ IRS የመጣን ነን በማለት የእርዳታ ገንዘቡን ለማስገባት የሰውዬውን የባንክ ሂሳብ ቁጥር ይፈልጋሉ። ግን ልዩ የገንዘብ እርዳታ የለም። እንዲሁም አንድ ሰው በስጦታ ካርድ፣ ገንዘብ በማስተላለፍ፣ በክፍያ መተግበሪያ ወይም በክሪፕቶ ገንዘብ እንዲከፍሉት ቢነግርዎት — በስደት ሁኔታዎ ወይም በማንኛውም ምክንያት እርስዎን ለመርዳት — ያም ማጭበርበር ነው።

### ማወቅ ያለብዎት፡-

- ስደተኛ ከሆኑ እና አንድ ሰው ስለ መንግስት እርዳታ ለማውራት ከቀረብዎት፣ በመልሶ ማቋቋሚያ ኤጀንሲ ውስጥ ያለውን የጉዳይ ሥራ አስኪያጅዎን ወዲያውኑ ያነጋግሩ።
- ለኢሚግሬሽን ላገኙት እርዳታ በስጦታ ካርድ፣ በገንዘብ ማስተላለፍ፣ በክፍያ መተግበሪያ ወይም በክሪፕቶከረንሲ በጭራሽ አይክፈሉ። ከአጭበርባሪ ጋር እየተነጋገሩ ነው።
- ተጨማሪ የስደተኞች መረጃ በUSCIS ድህረ ገጽ ያግኙ፡ ጥያቄዎች እና መልሶች፡ ስደተኞች።

## እውነተኛ እርዳታ ያግኙ

የሚረዳዎትን ትክክለኛ ሰው መምረጥ ትክክለኛውን ቅጽ መሙላት ወይም በትክክለኛው መንገድ መሙላት ያህል አስፈላጊ ነው። እንደ ጓደኛ ወይም የቤተሰብ አባል ያሉና በኢሚግሬሽን ሂደት ሊረዱዎት የሚፈልጉ ሰዎችም እንኳን በኋላ ላይ ችግር ሊፈጥሩብዎ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል፣ በቅጾች የሚረዳዎት ሰው የጠየቁትን ሊጽፍ ወይም ሊተረጉም ይችል ይሆናል፣ ይሁን እንጂ እርስዎ ምን እንደሚሉ ወይም የትኞቹን ቅጾች እንደሚጠቀሙ ምክር ለመስጠት ብቁ ላይሆን ይችላል። ለስደት ሁኔታዎ የሚፈልጉትን እውነተኛ እገዛ ለማግኘት ጥቂት ጊዜ ይውሰዱ።

## ለማገዝ ስልጣን ያላቸውን ሰዎች ያግኙ

በዩኤስ የፍትህ ዲፓርትመንት (U.S. Department of Justice) እውቅና ላለው ድርጅት የሚሠራ ጠበቃ ወይም እውቅና ያለው ተወካይ ብቻ የህግ የኢሚግሬሽን ሂደት ምክር ይሰጥዎታል። ከእነሱ ጋር አብሮ መስራት እርስዎን ከሚያታልሉ ሰዎችም ለመጠበቅ ሊረዳዎት ይችላል።

- አንድ **ጠበቃ** በስቴቱ ውስጥ የሙያ ማህበር አባል መሆን አለበት። የመረጡት ጠበቃ ከማህበሩ ጋር ጥሩ አቋም እንዳለው ያረጋግጡ።
    - ነጻ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ያለው የኢሚግሬሽን ጠበቃ ለማግኘት፣ ይህንን በስቴት የቀረበውን ዝርዝር ከዩኤስ የፍትህ ዲፓርትመንት (U.S. Department of Justice) ይመልከቱ።

  - እንዲሁም በአከባቢዎ የኢሚግሬሽን ጠበቃን ለማግኘት ይህንን ዝርዝር ከአሜሪካ ኢሚግሬሽን ጠበቆች ማህበር (American Immigration Lawyers Association) ይመልከቱ። እነዚህ ጠበቆች ክፍያ ያስከፍሉዎታል።

- **እውቅና ያለው ተወካይ** ጠበቃ አይደለም ነገር ግን የኢሚግሬሽን ምክር የመስጠት ስልጣን የተሰጠው ሰው ነው። እነሱ የሚሰሩበት ድርጅት ክፍያ ሊያስከፍልዎ ይችላል።

  - እውቅና ያለው ተወካይ በ DOJ እውቅና ላለው ድርጅት መሥራት አለበት።
  - በ DOJ ድህረ ገጽ ላይ ባለው የ እውቅና እና ፍቃድ መስጫ ፕሮግራም (Recognition & Accreditation Program) ገጽ ላይ በአካባቢዎ ያሉትን እውቅና ያላቸውን ድርጅቶች ያግኙ።

## እራስዎ ያድርጉት

ከመረጡ፣ በኢሚግሬሽን ሂደቶች ውስጥ እራስዎን መወከል ይችላሉ። በ USCIS ድረገጽ ላይ የእኔን አማራጮችን አስስ (Explore My Options) የሚለውን ክፍል በመገምገም ይጀምሩ።

### ማወቅ ያለብዎት፡-

- የኢሚግሬሽን ቅጾች ነፃ ናቸው። ኦፊሴላዊ ቅጾችን ለማግኘት በጭራሽ አይክፈሉ። ምናልባት የተሟሉ ቅጾችን ለ USCIS ሲያስገቡ የማመልከቻ ክፍያዎችን መክፈል ሊኖርብዎ ይችላል።
- ጥያቄዎች ካሉዎት፣ በ USCIS ድረገጽ ላይ ያለውን መገልገያዎች(Tools) ክፍል ይጠቀሙ ወይም በ USCIS ከማጭበርበሮች መራቅ (Avoid Scams) ገፅ ላይ ተጨማሪ ግብዓቶችን ያግኙ።
- ኦንላይን ማግኘት የማይችሉትን መረጃ ከፈለጉ፣ በ 800-375-5283 ለ USCIS የግንኙነት ማዕከል ይደውሉ። (መስማት የተሳንዎት ከሆኑ፣ የመስማት እክል ካለብዎት ወይም የንግግር እክል ካለብዎት የጽሑፍ ስልክ (TTY) ቁጥር፡ 800-767-1833 ይጠቀሙ።)

## በስደተኞች ላይ የሚደረጉ ማጭበርበሮችን ሪፖርት ያድርጉ

እርስዎ ወይም የሚያውቁት ግለሰብ ከኢሚግሬሽን ጋር የተያያዘ ማጭበርበር እንዳጋጠመው ካዩ ወይም እርስዎ ካጋጠመዎት፣

- **የፌደራል ንግድ ኮሚሽን (FTC)** በ 877-382-4357። ቋንቋ ለመምረጥ 3ን ይጫኑ እና ከዚያ ለአማርኛ 0ን ይጫኑ - ወይም ወደ ReportFraud.ftc.gov ይሂዱ። ማጭበርበሩን ሪፖርት ሲያደርጉ፣ የሚመችዎትን ያህል ወይም ትንሽ ስለእራስዎ መረጃ ይስጡን። ወይም፣ ለ FTC ሪፖርት ለማድረግ የኢሚግሬሽን ጠበቃዎን ስም ወይም የህግ ድርጅታቸውን ወይም ኤጀንሲያቸውን ስም ለመጠቀም ይጠይቁት።

- **ለአካባቢዎ ወይም ለስቴት ባለስልጣናት ሪፖርት ማድረግዎ አስፈላጊ ነው**

ስለ የተለመዱ የኢሚግሬሽን ማጭበርበሮች ተጨማሪ መረጃ በ USCIS ድረገጽ ያግኙ።